ቁጥር. OFAG.F.05.1/1/13
ቀን. 15/8/12

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለ አቶ ደበሌ ቃበታ

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የኮሚሽን መ/ቤቱን የ 2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትን ይመለከታል።</u>

በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 14 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 4 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

<u>ግልባጭ</u>

ለክቡር አቶ ላቀ አያሌው

የገቢዎች ሚኒስትር

(ከ15 ገጽ አባሪ ጋር)

<u>አዲስ አበባ</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን

የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲተር ሪፖርት

ሚያዝያ/2012

አዲስ አበባ

የጉምሩክ ኮሚሽን
የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ
(ከ1/5/2011እስከ 30/5/2011)
ኦዲተር ሪፖርት

የጉምሩክ ኮሚሽን የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት የ6 ወር ሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኮሚሽን መ/ቤቱ የሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው1146/2011)ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽን መ/ቤቱ የ2011 በጀት ዓመት የ6 ወር ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደ.ቁ8.2/0125/12 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም እና (በደ.ቁ8.2/0509/12 መጋቢት 11 ቀን 2012 ዓ.ም የተስተካከለው) በተጻፈ ደብዳቤ ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ ሪፖርት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቱ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በኮሚሽኑ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ኮሚሽኑና 13 ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያቀረቧቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

የኦዲተር ሪፖርት

ኦዲቱ የተከናወነው የዲክላራሲዮን የበጀት ዓመቱን፣የግማሽ ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የኮሚሽን መ/ቤቱ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ተከናውኖ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል 4 ምዕራፍ 1 አንቀጽ 89 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ መሆን እንዳለበት እንዲሁም በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 4 ሀ እና ለ ላይ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት እና የመጫኛ የማራገፊያ የመንከባከቢያ ወጪዎችና ክፍያዎች ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ላይ 5% በመጨመር በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተካትቶ መሰላት እንዳለበት፣ በተጨማሪም በደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/492/08 በቀን 17/03/2008 እና ይህን ደብዳቤ ለማሻሻል በተላከው ደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/445/09 በቀን 01/06/2009 መሰረት የማጓጓዣ ወጪ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ እየተነጻጸረ መካተት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ***በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በአዋጁና በመመሪያዎቹ መሰረት ባለመሰራቱ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 12,454,446.26 መገኘቱ ፣

2. የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2/መ መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የእያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ (ECVS) ውስጥ የሚገኙ የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ያለው ልዩነት በማነስ ከ10% በላይ ከሆነ የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ተቀባይነት እንደማይኖረው ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአስመጪዎች በቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ እና በጉምሩክ ዳታ ቤዝ(ECVS) ውስጥ ያለው የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ልዩነታቸው ከ10% በላይ በመሆኑ ምክንያት በጉምሩክ ዳታ ቤዝ ውስጥ ባለው ዋጋ መሰረት እንዲስተናገዱ ባለመደረጉ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ *በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር ብር 18,170,752.44 መገኘቱ፣
3. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 102 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ *በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 1,808,606.92 መገኘቱ ፣
4. በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈሉት ወይም የሚከፈሉት ወጪዎችና ክፍያዎች በአስመጪው እንዲቀርብ ተደርጎ ወጪው በዚያ መሰረት መካተት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃ እና ማስረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 (ሐ) መሰረት ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋን 2% (ሁለት በመቶ) በመውሰድ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ይካተታል ብሎ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን *በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች* ዲክሌር ተደርገው የገቡ ዕቃዎች የኢንሹራንስ ወጪ ማስረጃ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው እንዲሁም የኢንሹራንስ ሽፋናቸው እስከ ኢትዮጲያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ መሆኑን የማያሳይ

በመሆኑና በመመሪያው መሰረት እንዲስተናገዱ ባለመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 1,092,538.79 መኖሩን፣

5. በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 ክፍል 4 ምዕራፍ 1 የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን በተመለከተ በአንቀጽ 101 ላይ እንደተመለከተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ከሀገር የሚወጡ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላው ስለዕቃዎቹ የቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን በተመዘገበበት ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጸውን የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመጠቀም ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡ ***በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት*** ግን አስመጪዎች ዲክሌር ባደረጉት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የመጓጓዣ እና የኢንሹራንስ ወጪ በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ ምጣኔ ተሰልቶ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ እንዲካተቱ በማድረግ ፈንታ ቀጥታ ዶላሩን እንደ ኢትዮጵያ ገንዘብ በማካተት የተሰሩ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 98,643.45 መኖሩ፣

6. የጉምሩክ አዋጅ 859/2008 አንቀጽ 109 በህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀርና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም ገቢም ሆነ ወጭ ዕቃ ቀረጥና ታክስ መክፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ***በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት*** ወደ ሀገር ከገቡ ዕቃዎች ከሚመለከተው የመንግስት አካል ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት ማስረጃ ሰነድ ሳይኖር ዕቃዎቹ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 32,979.41 መኖሩ፣

7. የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 ክፍል ሁለት አንቀፅ 5/ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ሀ በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ ከሚችሉ ምክንያቶች አንዱ ብዛት መሆኑን ይገልፃል፡፡ ነገር ግን በ3 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ገቢ እቃዎች በትክክለኛ ኪሎ ግራም (ክብደት) መጠን በመያዝ ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 837,872.08 መኖሩ፤

8. የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ (ሰ) የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የምርት ዘመኑ ባበቃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች አማልተው ማሳደስ እንዳለባቸው ይገልጻል፣ የምስክር ወረቀቱ

ሳይታደስ የምርት ዘመኑ ያለፈ ከሆነ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት መብት ለጊዜው ሊነሳ እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን እንዲሁም አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ (ሐ) እና አንቀፅ (18) ንዑስ አንቀፅ (ለ) የሚሰጠው የምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ለሶስት ዓመት ሁኖ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት በየአመቱ የሚታደስ መሆኑን ይገልጻል፡፡ አምራቹ በወቅቱ የታደሰ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነትን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ በሁለተኛ መደብ (ሀ) መሰረት እንዲስተናገድ ይደነግጋል፡፡የድሬደዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ግን አስመጪዎች በዲክላራሲዮን ቁጥር C-2080/18 እና C-1772/18 ከ2009 እስከ 2011 ሳያሳድሱ የተስተናገዱ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 1,956,797.07 መኖሩ፣

9. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 10-1(ሪ) በተደነገገው መሰረት በፁሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የዕቃ ዲክላራሲዩን አስፈላጊነቱ በባለስልጣኑ የሚወሰን ሆኖ ከዲክላራሲዮኑ ጋር የሚቀርቡ ደጋፊ ሰነዶች ዋና ቅጅዎቻቸው ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቅጅዎቻቸው በአባሪነት መቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የሚገቡ እቃዎች በአብዛኞቹ ዲክላራሲዮኖች ላይ የሚቀርበው የኢንሹራንስ ወጪ ደረሰኝ ዋና ቅጂ/ኦርጅናል ያልሆነ እና የኢንሹራንስ ሽፋኑ በትክክል ወደ ሀገር ለገባው ዕቃ የተገባ የኢንሹራንስ ሽፋን ወጪ ሳይሆን ለሌላ ገቢ ዕቃ የተከፈለን የኢንሹራንስ ሽፋን ወጪን ኮፒ በመጠቀም የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚቀርቡት አብዛኛው ዲክላራሲዮኖች የማሪን ኢንሹራንስ ፖሊሲ የሌላቸው በመሆኑ የኢንሹራንስ ወጪ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የተካተተው ትክክለኛ ባለመሆኑ የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 13,000,607.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

10. በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 እቃቸውን ባላነሱ አስመጪዎች እቃዎቹ እንደተተዉ በመቁጠር በሽያጭ ለማስወገድ በተወሰነው ውሳኔ እና በመመርያ 122/2009 አንቀፅ 8 የዝግ ጨረታ ስርዓት በሚከተለው ሁኔታ መፈጸም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህም በንዑስ አንቀፅ 1 በጨረታ ሰነዱ ለዝግ ጨረታ ሽያጭ የቀረቡ ዕቃዎች ናሙና ከሁለት ቀናት ለማያንስ ጊዜ ጨረታው በሚካሄድበት ቦታ ለተጫራቾች እይታ መቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት የተተው እቃዎች ሽያጭ የጨረታ አሸናፊው እቃዎችን በሚረከብበት ወቅት እቃው ከተጠቀሰው መጠን መጉደሉን በማመልከት ተመላሽ ገንዘብ የጠየቀ ሲሆን ቅርጫፍ ጽ/ቤቱ እቃው የጎደለበትን ምክንያት ሳያጣራ በተጠየቀውም መሰረት በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ለገዢው/ለአሸናፊው ተመላሽ ብር 1,140,225.00 አድርጉ የተገኘ መሆኑ፣

11. በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 17/1/ መሰረት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሀፍት መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶች እና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎችን ሁሉ ሲጠየቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ መልኩ ወዲያውን ማቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ *3 ቅ/ጽ/ቤቶች* ለኦዲት ስራ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን በተሟላ ሁኔታ ያላቀረቡ በመሆኑ በሰነዶቹ/በዲክላራሲዮኖቹ ላይ የተሰበሰበው ገቢ በድምሩ ብር 767,873,291.32 ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

12. የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ሰኔ 2004 ዓ/ም በወጣው መመሪያ አንቀጽ 8 (1 ሀ-ሐ) ላይ እንደተመለከተው ማንኛዉም የመንግስት ሠራተኛ ለስራ ጉዳይ ከመደበኛ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለሚያደርገዉ እንቅስቃሴ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት በፊት የሚንቀሳቀስ ከሆነ እና ከስድስት ሰዓት ተኩል በኋላ የሚመለስ ከሆነ ለምሳ እንዲሁም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ የሚመለስ ከሆነ የእራት እንድሚታሰብለት መመሪያዉ ይገልፃል፡፡በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ማንኛውም የመንግስትመ/ቤት ክፍያ መፈፀም ያለበት ላገኘው አገልግሎት ወይም ለገዛቸው ዕቃዎች መሆን እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ፣

➢ የሥልጠና ተሳታፊዎች ፊርማ፣የውሎ አበል ፎርምና የትራንስፖርት ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ	579,818.30
➢ ለመ/ቤቱ የሚሰጠው ጥቅም ሳይኖር በጀት ላልተፈቀደለት የስፖርተኞች አልባሳት የተፈጸመ ክፍያ	78,389.67
➢ በብልጫ የተከፈለ የግዥ ሂሳብ	205,104.00

- መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ የተከፈለ የቤትአበል 61,000.00

በድምሩ ብር 719,207.97 ያለአግባብና በብልጫ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

13.የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች አንቀጽ 9 ስር በተዘረዘረው መሰረት እቃው ወይም አገልግሎቱ እንዲገዛ ትእዛዝ መሰጠቱ፣ እቃው ወይም አገልግሎቱ ተፈላጊውን ባህርያት ያሟላ ስለመሆኑ፣ እቃው ወይም አገልግሎቱ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን መግባቱን፣ የእቃውን ወይም የአገልግሎቱ ትክክለኛነት በሚመለከታቸው ባለሞያዎች የጽሑፍ ማረጋገጫ መሰጠቱ፣ በስምምነት መሰረት ቅድሚያ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ በውሉ ላይ በተጠቀሰው መሰረት መሆኑን፣ ለተገዛ እቃ ወይም አገልግሎት በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጅናል ደረሰኝ መሆኑን እና የእቃው ልዩ ባህሪ ምክንያት ወደ መጋዘን ማስገባት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እቃው መገዛቱ አግባብ ባለው ሰራተኛ ተረጋግጦ ክፍያ እንደሚፈፀም ይገልጻል፡፡ ነገር ግን

- ንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል19) ያልቀረበለት ወጪ 207,474.44
- ማስረጃ(ኢንቮይስ) ያልቀረበለት 10,145.00
- የህገ ወጥ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ሳይቀርብ የተከፈለ የጠቋሚ አበል 143,512.95

በድምሩ ብር 361,132.39 ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

14.በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 56/1 እና 2 መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ቢያንስ ሶስት አቅራቢዎች በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝ እንዳለበት እና አማራጭ እስካለ ድረስ በተደጋጋሚ የተወሰነ አቅራቢ መጋበዝ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም ሰኔ 2/2002 የወጣው መመሪያ ክፍል 5 ተራ ቁጥር 24.1 እና ታህሳስ /2008 ተሻሽሎ በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድመው ማቀድ እስከቻሉ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ሆኖም ግን ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይንም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዋጋቸው ከብር 200,000.00 በታች ለዕቃ ግዥ እና ከብር 150,000.00 በታች የአገልግሎት ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መግዛት የሚቻል መሆኑን ላይ ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ፣

- በ5 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከመመሪያው ውጪ ካለ ምንም ውድድር ከአንድ ድርጅት/ አቅራቢ ግዥ በመፈጸም ብር 2,013,753.32 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣

- በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ እና በተለያየ ጊዜ ግዥን በመከፋፈል ግዥ የተፈጸመ ብር 1,652,785.47 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

15. በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 92/1/ሀ ና ለ እና 4 መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ማንኛውም ድርጅቶች ከብር 10,000.00 በላይ እቃ ግዢ ሲፈጽሙ እና ከብር 3,000.00 በላይ የአገልግሎት ግዢ ሲፈጽሙ ቅድመ ግብር 2 በመቶ ቀንሰው ማስቀረት እንዳለባቸውና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው አካላት (30%) ቅድመ ግብር ተቀናሽ መደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ *በ 4 ቅ/ጽ/ቤት* ግዥ በተፈፀመበት ወቅት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የቅድመ ግብር ተቀናሽ ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ በተፈጸሙ ብር 24,066.25 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

16. የወሮታ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀፅ 26 የወሮታ ክፍያ ፈጻሚ ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ጉዳዮች ንኡስ አንቀጽ 1 (ሐ) መሰረት የሀብት አስተዳደር ወይም የፋይናንስ እንደ ጉዳዩ አግባብነት ወረታ ተቀባዩ ጠቋሚ፤ ያዥ፤ ተባባሪና ደጋፊ ለመሆኑ በባለስልጣኑ የተሰጠውን ማስረጃ ዋና ቅጅ መቀበልና ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳለበት፣እንዲሁም በአንቀፅ 18 በቀረጥ ነፃ ወይም በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ መብቱ በሌላቸው ሰዎች ወይም ድርጅት ይዞታ ስር ሆኖ የተያዘን ዕቃ እንዲሁም መብቱ ኖሯቸው ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጪ ሲገለገሉበት የተገኘውን እቃ በተመለከተ የሚከፈለው የወሮታ መጠን እንደ አግባብነቱ ዕቃው በተላለፈበት ጊዜ ወይም ዕቃው የተላለፈበትን ጊዜ በትክክል ማወቅ የማይችል ሲሆን ዕቃውን ወደ አገር ውስጥ በገባ ጊዜ ሊከፈል ይገባ ከነበረው ቀረጥና ታክስ ላይ ለጠቋሚ ሃያ በመቶ (20%) ፣ለያዥ ድጋፍና ትብብር ላደረገ አስር በመቶ (10%) እና እቃው የተያዘው በህግ አስከባሪ አካል ሲሆን ለተቋሙ ሰላሳ በመቶ (30%) የወሮታ ክፍያ ይከፈላል በማለት ቢያዝም፣

- በህገ ወጥ መንገድ ለተያዘ ንብረት ተባባሪ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሳይኖር የተከፈለ የወሮታ አበል	236,270.76
- በብልጫ የተከፈለ የወሮታ ክፍያ	38,831.50
- ያለአግባብ የይርጋ ጊዜ ላለፈበት የወሮታ ክፍያ ብር	167,553.84

- ከሞዴል 265 ጋር በማይናበቡ እና ትክክለኛ ባልሆኑ የክፍያ መጠየቂያዎች መሰረት የተፈጸመ የጥቆማ አበል 377,469.29

በድምሩ ብር 820,125.39 ያለአግባብና በብልጫ የተከፈለ የወሮታና የጥቆማ አበል መገኘቱ፣

17. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 6/6/ለ መሰረት የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሳቦች በዕለቱ በፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ መዝገብ ላይ መዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ዜሮ ሆኖ ሳለ በጥሬ ገንዘብ ጉድለት (4202)መያዝ ሲገባው በእጅ ያለ ወይም በሳጥን የሚገኝ (4101) ተብሎ የተመዘገበ በመሆኑ 4202 በማነሰ እና 4101 በብልጫ በብር 81,103.05 መታየቱ፡
18. የፖስታ ጥቅል ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸምን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 38/2002 ክፍል 2 አንቀፅ 5 ን/አንቀፅ 5 የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ከባለስልጣን መ/ቤቱ የተረከባቸውን ጥቅል ዕቃዎች ላይ የሚወሰነውን ቀረጥና ታክስ በመሰብሰብ ዕቃውን ለተቀባዩ ያስረክባል እና በዚሁ አንቀፅ ን/አንቀፅ 4 መሰረት በቂ ዋስትና ማስያዙን፣ የፖስታ ጥቅል ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም መግባቢያ ሠነድ አንቀፅ 3 ን/አንቀፅ 3.1.4.1 ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተብለው ለተለዩ የቀረጥና ታክስ መጠኑን በማስላት በፖስታ አገልግሎት ድርጅት ስም በተሰብሳቢ ይመዘግባል እንዲሁም ን/አንቀፅ 3.2.6 ቀረጥና ታክስ መግለጫ ከተዘጋጀለት ቀን ጀምሮ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ከተቀባዩ የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ለባለስልጣኑ ባንክ አካውንት ገቢ ያደረገበትን ሠነድ ለጉምሩክ በማሳወቅ ተመዝግበው የተያዙ ሂሳቦችን ያወራርዳል፣ በተጨማሪ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት በጊዜ ገደቡ የማይወራረድ ሂሳብ ከሆነ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ሆኖም የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ሆኖም በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ከፖስታ አገልግሎት ድርጅት በተሰብሳቢ ሂሳብ የያዘው ብር 21,842,956.96 በገቢና በተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ ላይ ባለመካተቱ የሂሳብ ሪፖርቱ በሁለቱ ሂሳቦች በማነስ እንዲያሳይ መሆኑ፣
19. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲኖረውና የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ መሰብሰብ እንዳለበት ቢገልጽም፣

- *በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች* ግን ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ብር 4,323,748.65 ተሰብሳቢ ሂሳብ በመኖሩ ተሰብሳቢ ሂሳብ በሪፖርቱ በብልጫ ማሳየቱ፣
- *በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች* ደግሞ ማስረጃ የሌለው ብር 99,895,437.25 የተከፋይ ሂሳብ በብልጫ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-19 በተገለጹት ሁኔታዎች ምክንያት የኮሚሽኑ የ2011 በጀት ዓመት የተጠቃለለው ሂሳብ የሂሣብ ሪፖርቶች የመ/ቤቱን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት አመቱን የስራ እንቅስቃሴ በሚያሳይ ሁኔታ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንዲሁም በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት ያልተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት ትክክለኛውን ሁኔታ አያሳይም፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር

ቀን---------------------------------

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ምንም እንኳን የኦዲት አስተያየታችንን ሊያስለውጡ ባይችሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና አፋጣኝ የእርምት እርምጃ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

1. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 51(1) ላይ እንደተደነገገው ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ትንንሾ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነስርአት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ድክሌር ተደርገው ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ቀረጥና ታክሳቸው የተሰላ(assessed) ቢሆንም በድምሩ ብር 29,383,342.62 ቀረጥና ታክሱ ሳይሰበሰብ ወይም አስፈላጊው እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱ፣

2. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ነገር ግን በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች አስመጪዎቹ በየቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን ቀረጥና ታክሳቸው በገቢ ዕቃዎች ቡድን ሳይሰላላቸው /Assess ሳይደረግ/ ዲክላራንቱ ያቀረበው የቀረጥና ታክስ መጠን በድምሩ ብር 35,218,926.60 ተመዝግቦ(registered) የተያዘ ቢሆንም ትክክለኛ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ /Assess/ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ፣
3. በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 (1 እና 2) መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለእዳ በ30 ቀናት ውስጥ እዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት ነገር ግን በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለእዳ ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚችል ይህንን በማይፈጽም ላይ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በየቅ/ጽ/ቤቱ በ 2011 በጀት ዓመት የታየው የእዳ መጠን እና በባለፉት አመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ በዋና ኦዲተር መ/ቤት አስተያየት የተሰጠበት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ሳይሰበሰብ የቆየ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ *በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 2,003,341,714.49 መኖሩ፣
4. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 71 እና 73 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ወይም በቦንድ ያስያዘዉ ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ወይም ዋስትናው መታደስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ *በ*

6 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 54,613,133.01 ዋስትናው ያልታደሰ ወይም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ መሆኑ፣

5. የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 107/2007 አንቀጽ 20/2/ሀ-ሠ/ በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ መሰረት ሂደቱን ጠብቆ ቅሬታው ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ፣በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጸ/ቤት
   - የ38 ድርጅቶች/ተግልጋዮች/ ለግብር ይግባኝና ለዋናው መ/ቤት ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ቢሄዱም አቤቱታ ጉዳያቸው ያለበት ሁኔታ የማይታወቅ ብር 519,391,640.24 መኖሩ፤
   - የ38 ግብር ከፋዮች በግብር ይግባኝና በዋናው መ/ቤት አቤቱታ ላይ ያሉት ከመቼ ጀምሮ ቅሬታ እንዳቀረቡ ቀን የሌላቸው በመሆኑ ቅሬታው ውሳኔ ሳያገኝ የዘገየበትን ቀን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፡፤

6. የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 107/2007 አንቀጽ 20/1/ሀ-ሐ/ እና 2/ሀ-ሠ/በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ መሰረት ሂደቱን ጠብቆ ቅሬታው ውሳኔ መሰጠት እንደለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በኮሚሽኑ ስር የሚገኙ ተገልጋዮች በተለያየ ጊዜ የተወሰነባቸውን ሂሳብ እና የውርስ ሂደት በመቃረን የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስለ መታየታቸውና ወቅቱን ጠብቆ ውሳኔ ስለ መሰጠቱና በውሳኔው መሰረት እርምጃ መወሰዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤
   - ከቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 13 ድርጅቶች እና ከሞጆ 1 ድርጅት ለኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ የተላኩ ቅሬታ አቅራቢዎች ዝርዝር መረጃ በቅ/ጽ/ቤቶች ቢኖርም በኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ መረጃ ተጣርቶ በክፍሉ መረጃቸው የሌለ እና አቤቱታቸው ያለበት ደረጃ የማይታወቅ ብር 155,263,446.82 መኖሩ፣
   - የአ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፤የአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤የሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፤የባህር ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

እና የድሬ ደዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስር ያሉ አስመጪዎች ለጉምሩክ ኮሚሽን አቤቱታ አጣሪ አቤቱታ አቅርበው በኮሚሽኑ ውሳኔ የተሰጠባቸው ቢሆንም በቅርጫፍ ጽ/ቤቶች ውሳኔ እንዳልተሰጠባቸው የተያዙ ድርጅቶች በመኖራቸው ከድርጅቶቹ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ብር 164,132,221.66 ያልተሰበሰበ መሆኑ፡፡

7. የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 107/2007 አንቀጽ 20/2/ሀ-ሠ/ በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ መሰረት ሂደቱን ጠብቆ ቅሬታው ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ አስመጪዎች ለኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ወቅቱን ጠብቆ ውሳኔ ስለመስጠቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤
   - ከቃሊቲ ጉምሩክ 4 ድርጅቶች እና በአዳማ ጉምሩክ 1 ድርጅት ለኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ አቤቱታ አቅርበው በመመሪያው መሰረት ቅሬታቸው በወቅቱ ሳይታይ ወይም ውሳኔ ያልተሰጠው ከ9 ወር እስከ አንድ ዓመት ከ5 ወር የዘገየ ቀረጥና ታክስ ብር 58,492,927.06 መኖሩ ፡
   - በኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ አቤቱታ ላይ ናቸው የተባሉት 5 ድርጅቶች መቼ አቤቱታ እንዳቀረቡ ቀን የሌላቸው በመሆኑ ቅሬታው ውሳኔ ሳያገኝ የዘገየበትን ቀን ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፡
   - በኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ወደ ግብር ይግባኝ የሄዱ ድርጅቶችን ዝርዝር እንዲሁም ውሳኔ ተሰጥቷቸው በንብረት መያዝ ወይም የንብረት እግድ ላይ ያሉ ድርጅቶችን ዝርዝር ያላገኘን መሆኑ

8. የኮሚሽን መ/ቤቱ በ2011 በጀት ዓመት የ6ወር የተመደበለትን የካፒታልና የመደበኛ ወጪ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ባለማዋሉ ለመደበኛ ወጪ ከተያዘው በጀት ብር 246,238,598.41 (25) ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ፣

9. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብና አንቀጽ 5 ከሀ-ሠ የተከፋይ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ መሰብሰብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ፣
    - በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በጊዜ ገደቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ከአንድ ወር እስከ ሰባት ዓመት የመሰብሰቢያ ጊዜው ያለፈበት ተሰብሳቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 443,906.25 መኖሩ፣
    - *በ1 ቅ//ቤት* ሰኔ 30/2011 በወቅቱ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ ብር 3,247,290.09 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡